# በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክመንግሥት

# አቅም ግንባታ ቢሮ

## የ1999 ዓ/ም የአፈጻጸም ሪፖርት

ሰኔ 1999

<u>አዋሳ</u>

# <u>የአቅም ግንባታ ቢሮ የ1999 ዓ.ም.</u>

# <u>ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት</u>

በሚቀጥሉት አስር ዓመታት በክልሉ የተቀናጀ ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም በመገንባት ድህነትና ኋላቀርነትን በፅናት የሚዋጋ በሁለንተናዊ መልኩ የመፈፀም አቅም የጎለበተ አመራር፣ ሲቪል ሰረቫንትና የሲቪክ ማሕበረሰብ ተፈጥሮ ማየት የሚለውን ስትራቴጂክ ራዕይ መሠረት በማድረግ በሴክተሩ ባሳለፍነው ዓመት ሊሰሩ ከታቀዱት ተግባራትና ግቦች ዋና ዋናዎቹየአቅም ግንባታ ኘሮግራሞችን በተቀናጀና በተጠናከረ ሁኔታ ለመፈጸም የቻሉ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳና ከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች መፍጠር የአቅም ግንባታ ኘሮግራሞችን አፈጻጸም ለማጠናከር 7 መመሪያዎችና ማኑዋሎች ማዘጋጀት፣ የኘሮግራሞችን አፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ የተገልጋዮች ፍላጎት ለማሟላት በቢሮው የአሰራር ሥርዓት ማሻሻያ መተግበር፣ የቢሮውን የሰው ሃይል ማሟላት፣ ከክልል እስከ ወረዳ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋት፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የሥራ አፈጻጸምና አመራር ሥርዓት የተዘረጋላቸው ወረዳዎች መፍጠር፣ በመንግሥት ፖሊሲና ስትራቴጂ ግንዛቤአቸው የጎለበተ አመራሮች ወጣቶችና ሴቶችን ማብቃት፣ የተቀናጀ የሲ/ሰ/ማ/ኘሮግራም አፈጻጸም ትግበራና የአመለካከት ለውጥ ማምጣትና በሴክተሩ እቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም ውስጥ የሥርዓተ ፆታ ኤች/አይ/ቪ/ ኤድስ ጉዳዮችን ማካተት ተጠቃሾች ናቸው፡፡

እነዚህ ግቦች የሴክተሩን ራእይና ዓላማ በተለይም ልማታችን ከማፋጠንና መልካም አስተዳደርን የማስፈን ተልእኮአችንን ከማሳካት አንፃር ሊኖራቸው የሚችለውን ተፅዕኖ ያገናዘበ የትኩረት መስኮችን በመለየትና ቅደም ተከተሎችን በማስቀመጥ የተለያዩ ተግባራት ተፈፅመዋል፡፡ የተሰሩ ሥራዎችም ዝርዝር አፈጻጸም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

# 1. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም

## 1.1 የአቅም ግንባታ ፕሮግራም በተቀናጀና በተጠናከረ ሁኔታ መተግበር የሚችል የማስፈጸም አቅም መገንባት ፣

የአቅም ግንባታ ኘሮግራሞችን በተቀናጀና በተጠናከረ ሁኔታ መፈጸም የቻሉ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳና ከተማ አመራሮችን ለመፍጠር ከተሠሩት ሥራዎች ውስጥ ተጠቃሹ ሥልጠና ነው:: በዓመቱ ለ80 የክልል አመራር አካላት በአፈጻጸም ክህሎት ማሳደጊያ ስትራቴጂክ እቅድ፣ በመልካም አስተዳደር በሥራ አመራርና በውጤት ተኮር አዘገጃጀት ምዘና ላይ ሥልጠና ተሰጥቷል:: የሰለጠኑት ሃላፊዎች በሙሉ በየመ/ቤታቸው ያለውን ባለሙያም እንዲያሰለጥኑ ተደርጓል:: በተመሳሳይ ሁኔታ የሁሉም ዞኖችና ልዩ ወረዳዎ እንዲሁም በተነጻጻሪ ሰፋ ያለ አምስት ከተሞች 95 የሚሆኑ የአቅም ግንባታ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በሲቪል ሰርቢስ 5ቱ ንዑሳን ኘሮግራሞችና ተዛማጅ አመራር ጥበቦች ላይ የአሰልጣኞች ሥልጠና እንዲወስዱ በማድረግ እነሱም በዞንና በወረዳ ደረጃ ያሉትን የመንግሥት ሠራተኞች በማሰልጠናቸው የሪፎርሙን አፈጻጸም መልሶ የሚነቃቃበት መንፈስና የነበረው የእውቀትና የክህሎት ክፍተት ለመሙላት ያስቻለ ትግበራ ተፈጽሟል:: ሥልጠናው ተቀዛቅዞ የነበረውን የማሻሻያ ፕሮግራም ትግበራ ተመልሶ ከማቀጣጠል አንጻር ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል::

በመሆኑም በክልሉ ሁሉም ዞኖች ፣ ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር ሴክተር መ/ቤቶች የሪፎርሙ ሥራ በ1999 ዓ/ም በተሻለ መነቃቃትና አፈጻጸም በመከናወን ላይ እንደነበረ መረዳት ተችሏል ::

በበርካታ መ/ቤቶች የ Quick wins ሥራ እየተከናወኑ ሲሆን በውጤት የመለካት ሥራም በተወሰኑ መ/ቤቶች ተግባራዊ በመሆን ላይ ይገኛል :: በቀጣይም በሁሉም የክልሉ ሴክተር መ/ቤቶች ወጥ በሆነ አሰራር ተግባራዊ ለማድረግ አደረጃጀትና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ተሰራጭተዋል ::

የአገልግሎት ሥርዓታችን ያሉበትን ችግሮች በመሠረቱ በመቀየር ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ታስቦ ባለፉት ዓመታትና በያዝነው ዓመት መጀመሪያ ልንፈጽመው የነበረው መሠረታዊ የአሰራር ለውጥ ተግባር ሰፋ ያለ

የግንዛቤ እጥረት የነበረበት መሆኑ በሂደት በመረጋገጡ ተግባሩን በተሟላ ግንዛቤ መጀመር ይቻል ዘንድ ከክልሉ የተመለመሉ 10 ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በደብረዘይት ሥራ አመራር ተቋም ሥልጠና እንዲወስዱ የተደረገ ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞም ከፌዴራል መንግሥት በመጡ አሰልጣኝ ከክልሉ ከፍተኛ አመራር ጀምሮ ለ90 ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በአዲስ መልክ ሥልጠና የመስጠት ሥራ ተከናውኖ በአዲሱ ግንዛቤ መሠረት በሚቀጥለው ዓመት የተሟላ የአሰራር ሥርዓት ለውጥ የሚሰራላቸው መ/ቤቶችና ለተግባሩ የሚያስፈልግ የሰው ሃይል በመለየት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተጠናቀዋል።

በዚሁ መሠረት ከየመ/ቤቶቹ ለተውጣጡ የReengineeringቡድን አባላት ስልጠና በመስጠት ወደ ጥናት ሥራው እንዲገቡ ተደርጓል ።

## 1.2 <u>የአቅም ግንባታ ፕሮግራምን ለማጠናከር የሚያግዙ 7 መመሪያዎችና ማንዋሎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ሆነዋል ።</u>

የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራምን አፈጻጸም ለማጠናከር ያግዛሉ ተብለው የታመነባቸው የስትራቴጂ እቅድና ሥራ አመራር፣ የአሰራር ሥርዓት ለውጥ፣ የተቋም፣ የሥራ ክፍልና የሰራተኛ ውጤት ተኮር፣ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘ ሮግራሞች ቅንጅታዊ አፈጻጸም፣ በአፈጻጸም ላይ የተመሰረተ ክፍያ ሥርዓትና የፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም አፈጻጸም መመሪያና ማኑዋሎች ተዘጋጅተው በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

## 1.3 <u>በማሻሻያ ፕሮግራሞች የተሰጡ ስልጠናዎች ፋይዳ (ለውጥ) ጥናት ተጠናቋል ።</u>

በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራም የጥናት ውጤቶች የተሰጡ ሥልጠናዎች ያመጡት ለውጥ /ፋይዳ/ እና የወደፊት ሥልጠና ፍላጎት ጥናት በታቀደው መሠረት ተፈጽሟል። ጥናቱ በማሻሻያ ትግበራው የተሰጡ ሥልጠናዎችን ችግርና መወሰድ ለሚገባቸው ርምጃዎች ጠቃሚ ግቦች ሆኗል። በተጨማሪም በቀጣይ ያሉትን የሥልጠና እቅድ ለማዘጋጀት መነሻ ማግኘት ተችሏል።

## 1.4 አምስቱን ንዑሳን ፕሮግራሞች አቀናጅቶ ለመተግበር አደረጃጀት ተፈጥሯል ፡፡

አምስቱ የሲ/ሰ/ማ/ኘሮግራም ንዑሳን ኘሮግራሞች አቀናጅቶ ለመፈጸም እንዲቻል የንዑሳን ፕሮግራም አስቀጣይ መ/ቤቶችን ያካተተ አደረጃጀት ተፈጥሮ ሥራው ጀምሯል፡፡ አደረጃጀቱ የየመ/ቤቱን ሃላፊዎች ያካተተ ስትሪንግ ኮሚቴና በሥራቸው ያሉ ባለሙያዎችን ያካተተ የቴክኒክ ኮሚቴ ያለው ሲሆን አደረጃጀቱን እስከታችኛው እርከን ለማድረስ የሚያስችል መመሪያ ለዞንና ልዩ ወረዳዎች ተልኮ የማደራጀት ሥራው ተሰርቷል ፡፡ ወደ ተግባርም ተሸጋግሮአል፡፡ አደረጃጀቱ በአስተባባሪ ኮሚቴና በቴክኒክ ኮሚቴ የተዋቀረ ሲሆን ሥራ በጀመረበት አራተኛው ሩብ ዓመት ሁለት የአስተባባሪና አራት የቴክኒክ ኮሚቴ ስብሰባ በማድረግ ውሳኔዎቸ አሳልፏል፡፡ ውጤትን መሠረት ያደረገ የክፍያ አፈጻጸም ሥርዓት መመሪያ አዘጋጅቶ አጠናቋል ፡፡

## 1.5 በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም አፈጻጸም በሁሉም የአስተዳደር እርከን ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ ተካሄዷል፡፡

በሪፎርሙ አፈጻጸም ለዞንና ልዩ ወረዳ እንዲሁም ሴክተር መ/ቤቶች ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ ማድረግ በተቀመጠው እቅድ መሠረት በመጀመሪያውና 3ኛ ው ሩብ ዓመት ከክልል እስከ ከተማ አስተዳደርና ዞኖች የመስክ ጉብኝትና ክትትል ተደርጓል፡፡ በድጋፋዊ ክትትሉ በየደረጃው ከሚገኙ ሃላፊዎችና የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር ውይይት በማድረግ ሪፎርሙ በክልላችን የደረሰበት ደረጃ ላይ የተሻለ ግንዛቤ ከመፍጠሩም ሌላ በተግባር በሚያጋጥሙ ችግሮች ዙሪያ ወጥ የመፍትሄ አቅጣጫ በማስቀመጥ የተሻለ ትግበራ እንዲደረግ በጎ ድርሻ አበርክቷል ፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘም በተከታታይ አፈጻጸሙን ለመገምገም የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራሞች አፈጻጸም መከታተያ ቼክ ሊስት ተዘጋጅቶ ለክልል ቢሮዎች፣ ለዞን፣ ልዩ ወረዳና ከተማ አስተዳደሮች ተሰራጭቷል ፡፡ ቋሚ የክትትልና ግምገማ ሥራዎች ሥርዓት ተፈጥሯል ፡፡ ሴክተር ቢሮዎችና የከተማ አስተዳደሮች በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረትም የተለያዩ ሥልጠናዎች

ከመስጠታቸውም በላይ የሪፎርም ኘሮግራሙን የጥናት ውጤቶች ያካተቱ የተለያዩ የአፈጻጸም ማኑዋሎችና መመሪያዎች ታትመው ተሰራጭተዋል፡፡

## 2. የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ፡-

በክልላችን መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የፍትህ ሥርዓቱን ማሻሻያ ኘሮግራም ፈጥኖ ከመተግበር ውጭ መፍትሄ ማምጣት እንደማይቻል ይታወቃል፡፡ በዚሀ መሠረት የፍትሕ አስተዳደር ሥርዓቱን ለሕብረተሰቡ ተደራሽና የተፋጠነ ፍትህ ለመስጠት ከማስቻል አንጻር የወረዳ ዳኞችና አቃቢያነ ሕጎችን ቁጥር ማስፋት እንዲቻል አስፈላጊውን የቅድመ ዝግጅትና ምልመላ ሥራዎችን በማጠናቀቅ 301 ሰልጣኞች ሥልጠና በመውሰድ ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህ በኩል በክልሉ በሁሉም አካባቢዎች በሕግ የሰለጠነና የክልሉን ሕዝብ ቋንቋ የሚያውቁ ሰዎችን በተፈለገው መጠን ማግኘት ባለመቻሉ ከፍተኛ እጥረት ካለባቸው ቦታዎች በመጀመር በራሳችን የሕግ ሰዎች ለማስተማር የምንችልበት ሁኔታ መፍጠር እንዳለብን ሂደቱ አሳይቶናል፡፡ በሚቀጥለው ዓመትም 150 ባለሙያዎችን ለማሰልጠን በዕቅድ ተይዟል ፡፡

አሁን ተመልምለው በመሰልጠን ላይ በሚገኘው ቁጥር ላይ 400 በመመልመል ከምናሰለጥነው ወጭ እጥረቱን ከሚታይባቸው ዞኖች በመጀመር የፍትህ ሥርዓቱ ማሻሻያ ኘሮግራም አፈጻጸም የነበረበትን የአመራርና የተግባር ችግሮች በመገምገም የኘ ሮግራሙ አስተባባሪና የቴክኒክ ኮሚቴዎች አደረጃጀት አዲስ መመሪያ ተዘጋጅቶ የተቋቋመ ሲሆን የክትትል ሥርዓትም ተፈጥሮ በየደረጃው በተሰራጨ ቼክ ሊስት መሠረት በመከናወን ላይ ይገኛል ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ፈጻሚ አካላት የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራትን በተመለከተ በሚከተለው ሁኔታ ተፈጻሚ ሆነዋል ፡፡

### 2.1 የዐቃቢ ህግ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም

በወንጀል ምርራ ሂደት የነበሩ ችግሮችን ለማስቀረት ከፖሊስ ጋር ተቀራርቦ በቅንጅት በመሥራት ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ክስ መመስረት የሚቻልበት ስልት ተቀይሷል ፡፡ በተለይም ከባድ ወንጀሎች ሲከሰቱና ከፖሊስ አቅም በላይ

ሲሆን በቀጥታ በመግባት ምርመራው ከፖሊስ ጋር እንዲሰራ ተደርጓል። ለአብነት በጌዲኦ ዞን በተፈጠረው ችግር ብቃት ያላቸው የህግ ባለሙያዎች ከፖሊስ ጋር በጋራ የምርመራ ሥራ ሰርተዋል ።

የምርመራ መዝገብ ተጠናቆ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ ክስ መመስረት እንደለበት የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት የሚደነግግ ቢሆንም በሪፎርሙ የአሠራር ለውጥ በማድረግ በአምስት ቀን ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል ። ይህም የሪፎርሙ እንቅስቃሴ ውጤት መሆኑን የሚያመለክት ነው ።

የዐቃ ህግ ምስክሮችና የመከላከያ ማስረጃ አቀራረብ የፍትህ አሰጣጡን እንዲዘገይ የሚያደርግ በመሆኑ ነጻ ሊሆኑ የሚገባቸው ሰዎች የሚጎዱበት አሰራር በመቅረት ላይ ይገኛል ። የዐቃቤ ህግ ምስክሮችም በራሳቸው ወጭ ማስረጃ ለመስጠት ይመጡ የነበረ መሆኑ ቀርቶ አበል በመንግሥት ተሸፍኖ እንዲመጡ እየተደረገ ይገኛል ። ፍርድ ቤት ሲቀርቡ በዐቃቢያነ ህግና በዳኞች ይደረግባቸው የነበረ ማመናጨቅ እንዲቀር በመደረጉ ምስክሮች በነጻነት ያዩትን መመስከር እየቻሉ ናቸው ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የዐቃቤ ህግ ማስረጃ አቀራረብ ግድፈትን ለማስወገድ በተደረገው የአሰራር ለውጥ የማስረጃ ማካካስ ደንብ ቀጥቶ ተግባራዊ እንዲሆን በመደረጉ የዐቃቤያነ ህግና የመከላከያ ማስረጃዎች በአንድ ቀን የሚሰሙበት ሥርዓት ተፈጥሯል ። የዐቃቤያነ ግህ የክስ ግድፈቶችን የማስወገድ የዐቃቤ ህግን ሥራ በውጤት የመለካት ሥርዓት በክልል ደረጃ ተግባራዊ መደረግ በመጀመሩ በወንጀል ክስ አቀራረብ ቀደም ሲል የነበረው አሰራርና የግድየለሽነት ሥራዎች በመቀረፍ ላይ ናቸው ። የተዘዋዋሪ ችሎት ሥራዎችንም ለዞንና ለልዩ ወረዳ ዐቃቤ ህግ መዋቅር ውክልና በመስጠትና የባለጉዳዮችን የይግባኝ መመላለስ በማስቀረት ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ ተችሏል ።

የዐቃቤ ህግ ማስረጃና የመከላከያ ማስረጃን በአንድ ጊዜ ሰምቶ ፈጣን ውሳኔ መስጠት ተጀምሯል ። በማስረጃ አቀራረብ ችግር ያለባቸውን አቃቤ ህጎችን

በመተዳደሪያ ደንብ መሠረት የዲሲፕሊን እርምጃ እየተወሰደባቸው ይገኛል ፡፡ ይህም የተጠያቂነት መርህን በማጎልበት ላይ ይገኛል ፡፡

ማስረጃ ባለማሟላት የተንዛዛ የፍርድ ቤቶች ቀጠሮና የፖሊስ የጊዜ ቀጠሮ ችግር ተቃሎ ፈጣን ምላሽ እየተሰጠ ነው ፡፡ ይህን ለማስቀረት ከከፍተኛ ፍ/ቤት ፖሊስና ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን ጋር ውይይት ተደርጎ ፖሊስ ያለበቂ ምክንያት የጊዜ ቀጠሮ እንዳይጠይቅ ፣ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን በጥልቀት ሳመረምር የጊዜ ቀጠሮውን እንዳይፈቅድ ፣ ማረሚያ ቤቶችም በሀገርና ህዝብ ደህንነት ላይ አደጋ የሚያመጡ ወንጀለኞች ካልሆኑ በስተቀር ያለፍርድ እንዳይቀበል ዐቃቤ ህግም ፖሊስን መቆጣጠር እንዳለበት የጋራ መግባባት በመደረሱ ችግሩ እየተቀረፈ ይገኛል ፡፡

በወንጀልና ፍትሐብሔር ክስ አቀራረብ በተደራቢነት ያለማቅረብና የወንጀል ተሳትፎ የሌላቸውን ያለበቂ ማስረጃ ጥፋተኛ ለማድረግ ክስ ለማሻሻል በሚል ለፍርድ ቤቶች ይቀርብ የነበረ ጥያቄ አሰራሩ ተሻሽሏል ፡፡

የውልና ማስረጃ ፣ የማህበራት ምዝገባና ጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ማሻሻያን በሚመለከት ወራትን ይፈጅ የነበረው የማህበራት እውቅናና ጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ ወደ ስዓታት ዝቅ እንዲል ተደርጓል ፡፡

የፍትህ አካላትን አቅም ከመገንባት አንጻር በጋሞጎፋ ፣ በሲዳማ ዞንና ባላባ ልዩ ወረዳ በህገ-መንግሥታዊ መርሆችና የስልጣን ክፍፍል ፣ በሰብአዊ መብቶችና በመልካም አስተዳደር ስልጠናዎች ተሰጥተዋል ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ፣ በሴቶች መብቶች ፣ በአዲሱ የወንጀል ህግ እና የቤተሰብ ህግ ላይ ለ104 ወረዳዎች ስልጠና ተሰጥቷል ፡፡

የወንጀል ድርጊት ሰለባ የሆኑ ሰዎች ፣ጥቆማ አቅራቢዎችና የምስክሮችን ደህንነት ጥበቃና የህግ ከለላ የመስጠትና የካሳ ስርዓት መብት እንዲከበር እየተደረገ ሲሆን ምስክሮች ያወቁትን እውነታ በሚለውጡ ግለሰቦች ላይ ክሶ የማስቀጣት ሥራም እየተሰራ ይገኛል ፡፡

በወረዳና ዞን የሰው ሃይል እንዲሟላ ዲግሪ ያላቸው በፌዴራል ዲፐሎማ ያላቸው ደግሞ በክልሉ ለሁለት ዓመት ስልጠና እየወሰዱ ነው ፡፡ ከፖሊሲዎች ጋር እንዲተዋወቁም ለ500 ዐቃቤያነ ህጎች ስልጠና ተሰጥቷቸዋል ፡፡

## 2.2 <u>የክልል ምክር ቤት ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም</u>

የክልሉ ምክር ቤት የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አንዱና ወሳኝ የህግ አውጭ አካል ከመሆኑ አንጻር የቋሚ ኮሚቴ አባላት በየሩብ ዓመቱ እየተገኙ አፈጻጸሞችን የመገምገም ሥራ ተሻሽሎ የቋሚ ኮሚቴ አባላት ሰብሳቢዎች በመደበኛ ቋሚ ሠራተኛነት የሚሰሩበት ሁኔታ ያሰራር ሥርዓት ተፈጥሮ ገቢውን ሥርዓት በማከናወን ላይ ናቸው ፡፡ የም/ቤቱን ቋሚ ኮሚቴ አባላትና የዞንና የወረዳ ም/ቤት አባላትን የህግ ንቃት በማጎልበትና የመልካም አስተዳደር ፖኬጅ አፈጻጸም ግንቤአቸውን ለማስፋት ተደጋጋሚ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን ከአቻ ክልሎች ጋር የልምድ ልውውጥ ተደርጎ በጎ ተሞክሮ ማግኘት ተችሎል፡፡

## 2.2 <u>የፖሊስ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም</u>

የፖሊስ ሚና ወንጀል ከተፈጸመ በኋላ በምርመራ ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ ወንጀል ከመፈጸሙ በፊት ወንጀል ፈጻሚዎችንና የሚፈጸምበትን ቦታና ምክንያት አስቀድሞ በመለየት የመከላከል ስራ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የኮሚኒዩኒቲ ፖሊሲንግ ጽንሰ ሀሳብን መሠረት በማድረግ ወንጀልን በህብረተሰብ ተሳትፎ ለመቀነስና ፣ ወንጀልን ከህብረተሰቡ ጋር በጋራ ለመከላከል የሚቻልበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ እየሆነ ነው ፡፡

የመርማሪ ፖሊሶችን ብቃት ከማሳደግ አንጻር አጫጭርና ረጂም ጊዜ ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጎ ምርመራን በብቃት ከመምራት ባሻገር የተጠርጣሪዎችን ሰብዓዊ መብት ጠብቆ መረጃን ማግኘት ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራበት ይገኛል፡፡ ከዚህ ሌላ 257 መደበኛ የፖሊስ አባላት በመደበኛ ስልጠና እንዲመረቁ

የተደረገ ሲሆን 600 ከክልል እስከ ወረዳ የሚገኙ የፖሊስ የአመራር አባላት ደግሞ በተለያዩ የመንግሥት ፖሊሲዎችና መልካም አስተዳደር ፖኬጅ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል ፡፡ ለ11 አባላትም በመረጃና በመስክ አሰልጣኝነት የአጭር ጊዜ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የነቁ አባላትን ክህሎት በማሳደግ ብቁ አመራርን ለመፍጠር በቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ 74 አባላት በ10+3፣ 12 አባላት በማኔጅመንት፣ በICT እና በህግ በአርባ ምንጭና በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ በመማር ላይ ናቸው ፡፡ ለ30 ፖሊስ አባላት ከኖርዊይ መንግሥት ጋር በመተባበር በሰብዓዊ መብቶች ላይ ስልጠና ተሰጥቷል ፡፡ ለ150 አባላት ደግሞ ከቀይ መስቀል ድርጅት ጋር በትብብር ስለ ሰብዓዊ መብት ስልጠና ተሰጥቷል ፡፡ ለ585 አባላት ደግሞ የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ስልጠና ለሶስት ቀን ተሰጥቷል ፡፡

የፖሊስን አመራር የሚያጠናክሩ የሥነ-ምግባር ፣ የምልመላና ቅጥር፣ የዝውውር ፣ የምደባና የዲስፕሊን መመሪያዎችን በማውጣት ጸድቀው የሥራ መመሪያ እንዲሆኑ ተደርጓል ፡፡ በኢግዚቢት አያያዝ የግለሰቦች ንብረት እንዳይባክን ታስቦ ባለቤቱ የታወቀውን ንብረት ወዲያውኑ የመመለስ ሥራ እየተሰራ በመሆኑ አፈጻጸሙን ግልጽነትና ተጠያቂነትን የሚያጎለብት በመሆኑ በቀጣይም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል ፡፡

## 2.4 <u>የማረሚያ ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም</u>

ማረሚያ ቤቶች የእስረኞች ሰብዓዊ መብት ተጠብቆ ተገቢው የመጠላያ ፣ የምግብና የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙና አምራች ዜጋ ሆነው እንዲወጡ የሙያ ክህሎት ስልጠና እንዲሰጣቸው በማድረግ ይገኛል ፡፡

በዚህም መሠረት የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱን ለማሻሻል የተጠናከረ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ነው ፡፡ በፍርዱ አይነት እስረኞችን ለይቶ ማኖር ባይቻልም የወንድና የሴት እንዲሁም ህጻናት ተለይተው እንዲቆዩ እየተደረገ ነው፡፡

የማረሚያ ቤቶችን አገልግሎት ለማሻሻል ለአመራር አካሉና ለጠባቂ ፖሊሶቸ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች የተሰጣቸው ሲሆን የህግ ታራሚዎችን አያያዝ የዓለም አቀፍ ታራሚዎች ዝቅተኛ መስፈርት ለመያዝ እንዲያስችል ጥረት በመደረግ ላይ ነው ፡፡

በፍርድ ውሳኔ የተሰጣቸው ታሪሚዎችም በይግባኝ የመከራከር መብታቸውን ተጠቅመው ወደ ፍ/ቤት ቀርበው እንዲከራከሩ ተደርጓል ፡፡ በማረሚያ ቤቶች ያሉ እስረኞች መረጃ በዓይነትና በጾታ ተለይቶ በኮምፒውተር የመረጃ አያያዝ እንዲጎለብት ሥራው ተጀምሯል ፡፡ የታራሚዎችን ሰብዓዊ መብት ጥበቃን በተመለከተም በዓቃቤ ህግ በኩል በየጊዜው ጉብኝት ተደርጓል ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ከክልሉ ከሚገኙ 23 ማረሚያ ተቋማት ለተውጣጡ 500 አመራሮች በተለያዩ የህግ ሰነዶችና የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ላይ ጥልቀት ያለው ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል ፡፡

## 2.5 <u>የሚሊሺያ ንዑስ ፕሮግራም</u>

የሚሊሺያ ሀይል በህብረተሰቡ ውስጥ ተመልምሎ ከምርት ተግባሩ ሳይለይ የአካባቢውን ሰላምና ጸጥታ ከማስከበር ባሻገር የተለያዩ የመንግሥት ፖሊሲዎችን አፈጻጸም ተገቢውን ድርሻ ማበርከት ስላለበት ከፖሊስ ጋር ወንጀል የመከላከል ስራን እንዲሰሩ አጫጭር ስልጠናዎች በየወረዳው ተሰጥቷል ፡፡

የሚሊሺያ ሀይል በሥራ ላይ እያለ ለሚደርስበት ጎዳት የካሳ ክፍያ መክፈል የሚያስችል ደንብ ተዘጋጅቶ ለአስተያየት ቀርቧል ፡፡ ሌሎች የሥምሪትና የምልመላ መመሪያዎች ባይኖሩም በማቋቋሚያ አዋጁ መሠረት እየተሰራ ይገኛል፡፡

የሚሊሺያ ሀይል ሥራውን ከሌሎች ጋር በቅንጅት መሥራት ስላለበት ከፖሊስ፣ ከመከላከያና በቀበሌ ደረጃ ከብሔራዊ ተጠባባቂ ሃይል ጋር ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል ፡፡ በተለይም በተለያዩ ቦታዎች በተቋቋሙ የጸጥታ ኬላዎች በተከታታይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አስችሏል ፡፡

## 2.6 የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም

ልማዳዊና ዘገምተኛ የነበረውን የፍርድ አሰጣጥ በማስቀረት ቀልጣፋና ውጤታማ ፍትህ መስጠት እንዲቻል የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ተነድፎ ወደ ተግባር በመገባቱ ቀላል የማይባል መሻሻሎች ታይተዋል ፡፡

ከመዝገብ አከፋፈት ጀምሮ ይታዩ የነበረውን መጓተት ለማስቀረት እና የሥራ ፍሰት ሂደት ተገልጋይ ተኮር እንዲሆን የማሻሻያ ሥራዎች ተሰርተዋል ፡፡ መዝገቦች ከሠራተኛ ሠራተኛ እንዲሁም ከኃላፊ ኃላፊ በመምራት ለማጽደቅ የሚፈጀውን ጊዜ ለመቆጠብ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቷል ፡፡

የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ሥራዎችን ስኬታማ ለማድረግ ከሁሉም የፍትህ አካላት ጋር ውይይት ይደረጋል ፡፡ በክልል አቀፍ የፍትህ አካላት የምክክር ጉባዔ ለማቋቋም የደንብ ረቂቁ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ተዘጋጅቷል ፡፡

የጉዳዮች ክምችት ብዛትን ለመቀነስና የተፋጠነ ፍትህ ለመስጠት እንዲቻል ከሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ተመራቂ ተማሪዎች ጋር የተግባር ልምምድ ሥራዎች ተሰርተዋል ፡፡ የተከሰሱ ሰዎችን የመከላከል መብት ለመጠበቅ የተከላካይ ጠበቆች በየፍርድ ቤቱ እንዲሟሉ ሆኗል ፡፡ ለልምድ እንዲረዳ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተወሰኑ የፍርድ ውሳኔዎች ለሁሉም ወረዳ ፣ ዞንና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች እንዲደርሳቸው ተደርጓል ፡፡ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ውሳኔዎች አገር አቀፍ የፍትህ አሰጣጥ ወጥነትን ለማስፈን ግንዛቤ ስለሚሰጥ አስገዳጅነትን የሚደንግገው አዋጅ ለሁሉም ፍ/ቤቶች ተዳርሷል ፡፡

ወቅታዊ የቁጥጥር ክትትልና ግምገማ አሰራር በፍርድ ቤቶች ለማስፈን እንዲቻል በዞኖችና ወረዳዎች የመስክ ጉብኝት ሥራ ተሰርቷል ፡፡ የመዝገብና ውሳኔ ግልባጮች በተገቢው ፍጥነት ለባለጉዳዮች ለመስጠት ፎቶ ኮፒ ማሽኖች ለወረዳ ፍ/ቤቶች በማሟላት ላይ ናቸው ፡፡ የማመልከቻ ፎርሞች በፍርድ ቤቶች ተዘጋጅተው ለባለጉዳዮች እየተሰጡ ከመጉላላትና ከወጭ እንዲድኑ ተደርጓል ፡፡

የፍትህ አሰጣጥ አቅምን ለማጎልበት በርካታ ሥልጠናዎች የተሰጡ ሲሆን ልማዳዊና ዘገምተኛ አሰራርን ለማስቀረትና በሰብአዊ መብቶች ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር ለ150 ዳኞች ስለ ፍርድ ቤት ማሻሻያ በሁለት ዙር በቦንጋና በወላይታ ላይ ፣ በሥነ-ምግባር ማሻሻያ ላይ ለከፍተኛ ፍ/ቤትና ለወረዳ ፍ/ቤት ፕሪዘዳንቶች ከፕሪዝን ፌሎሽፕ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር ፣ በመረጃ አያያዝና ፋይል አያያዝ ከብሪትሽ ካውንስል ጋር በመተባበር ለከፍተኛ ፍ/ቤቶች መዝገብ ቤት ሠራተኞ በርካታ ስልጠናዎች ተሰጥቷቸዋል ።

በእጅ ይሰሩ የነበሩ የተከራካሪዎችና የምስክሮች ቃል እንዲሻሻል ለ6 ወረዳ ፍ/ቤቶች የኬዝ ሪኮርዲንግ ማሽን ወረዳዎቹ ባሳዩት መልካም የአፈጻጸም ብቃት በማበረታቻነት ተሰጥቷቸዋል ። ለ27 ወረዳዎችም ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ተጠቅመው መስራት እንዲችሉ ኮምፒውተሮች ከፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በተደረገ ድጋፍ ተሰጥቷቸዋል ። የፍርድ ቤቶች የጉዳዮች ፋይል አያያዝና ቀጠሮ የመስጠት ሥርዓት በዘመናዊ ዳታ ቤዝ ሲስተም በ25 ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ተግባራዊ በመደረጉ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ተችሏል ።

የፍርድ ቤትን ሥራ ተደራሽ ለማድረግ ተዘዋዋሪ ችሎቶች ቀጥለዋል ። አዲስ ቋሚ ችሎትም ተቋቋሟል ። የህግ ግንዛቤ ለማሳደግ የፍርድና ህግ መጽሄት ተዘጋጅቷል ። የፍ/ቤት ሥራን የሚገልጹ ብሮሸሮች ተሰርተዋል ። በኤፍ ኤም ደቡብ ፕሮግራም ሥርጭት ተጀምሯል ።

## 2.7 የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን

ኮሚሽኑ ሥራውን ከዐቃቤ ህግ ጋር ተመሳሳይ ሥርዓት ተከትሎ የሚሰራና ከምርመራ መምሪያ ጋርም በመሆን በመደበኛ ፖሊስ እንዲመረምር ውክልና በሚሰጠው ጉዳዮች ላይ ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ ነው ።

የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የምርመራ መዝገቡ በኮሚሽነርና በምክትል ኮሚሽነር መሆኑ ቀርቶ በመምሪያና በዳይሬክተር ደረጃ እንዲጠናቀቅ ተደርጓል ።

በአጠቃላይ በልዩ ልዩ አሥራ አራት ደረጃዎች አልፎ ውሳኔ ያገኝ የነበረው ጉዳይ በሰባት ዝቅ ብሎ ውሳኔ እያገኘ ነው ፡፡

በማስረጃ አቀራረብ በኩል የማስረጃዎች ደህንነት ጥበቃና ዋስትና ማግኘታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ምስክሮች ያወጡትን ወጭ ማካካሻ እንዲከፈል ተደርጓል ፡፡ በግልጸኝነትና ተጠያቂነት አንጻርም እያንዳንዱ አቃቤ ህግ በምርመራ መዝገብ አወሳሰን ፣ የችሎት ክትትል እንዲሁም የፍትሀብሄር ጉዳዮችን አፈጻጸም ሂደቱን ለመከታተል የሚያገለግሉ ቅጾች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ሆነዋል ፡፡

ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን ከማስፈን አኳያ የወንጀል ጉዳዮች አወሳሰን የራሱን አሰራር የዘረጋ ሲሆን የምዝገባ አወሳሰን ሥርዓት ፣ የችሎት መዝገብ አመራርና ክትትል ፣ የፍ/ሔር ጉዳዮች መከታተያ ፣ የሥራ አመራርና የመረጃ አያያዝ ሥርዓቶችን የሚያካትት ሆኖ ለእያንዳንዱ የአሠራር ሥርዓት ማንዋሎችና ቅጻ ቅጾች ተዘጋጅተው እየተሰራባቸው ነው ፡፡

በኮሚሽኑ የሙስና መከላከልና ምርመራ መምሪያ ከክልል ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት ጋር በመሆን ተለይተው በታወቁ የክልል መ/ቤቶች ጥናት በማድረግ ወንጀልን አስቀድመው የመከላከል ሥራን ለመጀመር ዝግጅቱ ተጠናቋል ፡፡

የአቅም ግንባታ ሥራን በተመለከተ ለ6 ባለሙያዎች ለሶስት ቀን ከፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ- ሙስና ኮሚሽን ስልጠና ተሰጥቷል ፡፡ 13 ባለሙያዎች በሲ/ሰ/ማ/ፕሮግራም ላይ ሰልጥነዋል ፡፡ በዞንና ወረዳ ለሚገኙ የፖሊስ የምርመራ ኃላፊዎችና መርማሪዎች የሙስና ወንጀል አመራመርን ብቃት ለማሳደግ በሶስት ማዕከላት 150 አባላትን ለማሰልጠን ፕሮጀክት ተቀርጾል ፡፡ በተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች ለበርካታ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ፎረም አባላትና የህብረተሰብ አባላት ስልጠና ተሰጥቷል ፡፡ ፖስተሮች ፣ ብሮሸሮችና መጽሔቶች ታትመው መየደረጃው ተሰራጭተዋል ፡፡

## 3. የወረዳ አቅም ግንባታ ፕሮግራም

የሴክተሩ ሌላው ትኩረት  የነበረው የወረዳዎችን አቅም በመገንባት  የማስፈፀም ብቃታቸውን ማሳደግ ነበር፡፡ በዚሁ መሠረት ከ25 ሺህ በላይ የዞን፣ የልዩ  ወረዳና የወረዳ ከተማ አስተዳደር አመራር አካላት በመንግሥት ፖሊሲ፣ ትስራቴጂና መልካም አስተዳደር ፓኬጅ ሰነዶች ላይ ሥልጠና በመስጠት ለተግባር የሚያግዝ ግንዛቤና የጋራ መግባባት መፍጠር ተችሏል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም ከ28000 በላይ  ለሚሆኑ የክልሉ ገጠር ቀበሌ አመራሮች ስለመልካም አስተዳደር፣ ሕብረተሰብ ተሳትፎና የመንግሥት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ላይ ከ3-5 ቀናት የፈጀ ሥልጠና በመስጠት የመልካም አስተዳደሩ ፖኬጅ ትግበራ ተጀምሯል፡፡

ያልተማከ የአካባቢ (የወረዳ) አስተዳደርን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአካባቢ አስተዳደር ረቂቅ ፖሊሲ፣ የሕግ ማዕቀፍና የወረዳ ዝቅተኛ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ሰነድ በውጭ ባለሙያዎችና ከክልሉ ከተለያዩ ሴክተሮች በተውጣጡ ባለሙያዎች ተዘጋጅቶ  ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር ውይይት ተደርጎበት የውይይቱን ግብረ መልስ ባካተተ መልኩ ተሻሽሎ  ቀርቧል፡፡ በቀጣይም ከፍተኛ  አመራሩ ተወያይቶ ለሚመለከተው አካል ለውሳኔ ያቀርበዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የወረዳ የማስፈፀም አቅምን ከማጎልበት አንጻር ያለውን የባለሙያ እጥረት ለማቃለል በዲኘሎማና በዲግሪ በርቀት ትምህርት 870 ባለሙያዎች በሲቪል ሰርቪስ  ኮሌጅ በተለያዩ ሙያዎችበመሰልጠን ላይ ሲሆኑ 250 ባለሙያዎችን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በርቀት ትምህርት ለማስተማር ቀደም ብለን ስምምነትና ክፍያ የፈጸምን ቢሆንም በዩኒቨርስቲው በኩል ባስከተለው አዝጋሚ አፈጻጸም ምክንያት ዘግይቶም ቢሆን በቅርቡ ትምህርቱን ለመጀመር የሚያስችል ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የወረዳ አቅም ግንባታ አፈጻጸም በዝርዝር ሲታይ የሚከተሉት ተግባራትም ተፈጽመዋል፡፡

1. በመንግስት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂዎችና በመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ሰነዶች ላይ ከ25500 በላይ ለሚሆኑ የዞንና የወረዳ አመራር አባላት፣ ከ2ኛ ዓመት በላይ ለሆኑ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ከ15-1 ወር  የቆዬ ስልጠና ተሰጥቶ ለቀጣይ ሥራ የሚያግዝ ግንዛቤና የጋራ መግባባት መፍጠር ተችሏል፡፡

2. ባልተማከለ የወረዳ አስተዳደር ፣ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችና በአቅም ግንባታ ሥራዎች ስለተገኙ ውጤቶችና ቀጣይ ተግባራት ላይ ከዞንና ከወረዳ ለተውጣጡ 108 አመራሮች ስልጠና ተሰጥቶ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል ።

3. ከ500000 በላይ ለሆኑ በክልሉ የገጠር ቀበሌዎች ለሚገኙ የተመረጡ አርሶ አደሮች ስለመልካም አስተዳደር መርህ ፣ ስለህብረተሰብ ተሳትፎና የመንግሥት የልማት ፖሊሲዎች ስልጠና ተሰጥቶ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ትግበራ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ተደርጓል ። የጋራ መግባባትም ተፈጥሮ ፓኬጅውን የመፈጸምና የማስፈጸም ድርሻቸውን በማበርከት ላይ ናቸው ።

4. ከዞንና ከልዩ ወረዳ ለተውጣጡ ባሙያዎችና ኃላፊዎች የአሰልጣኞች ስልጠና ሰለ ወረዳ መልካም አስተዳደር ፓኬጅ የተሰጠ ሲሆን ፣ እነዚህ አሰልጣኞች በዞንና በየልዩ ወረዳው ስልጠና እንዲሰጡ ተደርጎ ስልጠናው ተግባራዊ ሆኗል ።

5. በክልሉ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ስልጠና መመሪያ በአዲስ መልክ ተሻሽሎ ተጠናቋል። በ2000 ዓ/ም ተግባራዊ ይደረጋል ። ከዚህ ጋር ተያይዞም ልዩ ልዩ ቅጻቅጾች የተዘጋጁ ሲሆን በወረዳዎች የሚታየውን የሰለጠነ የሰው ሃይል ለመቅረፍ የሚያስችልና አዳዲስ የለወጥ ሀይል ሊሆኑ የሚችሉ ምሩቃንን በሚያሟሉበት የሥራ ደረጃ በዜሮ አገልግሎት ለመቅጠር የሚያገለግል መመሪያ ተዘጋጅቶ የተጠናቀቀ ሲሆን ከ2000 ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ ይደረጋል ። በተጨማሪም የወረዳዎች የሰለጠነ የሰው ሃይል ልማት ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት መረጃ የማሰባሰብ ሥራ ተከናውኖ የክልሉ የሰው ሃይል ስልጠና ፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነድ በመሠራት ላይ ይገኛል። የወረዳ አቅም ግንባታ ፕሮግራም አፈጻጸም ያለበትን ደረጃ ለመለካትና ወቅታዊም ሆነ ቀጣይ ድጋፍ ለማድረግ ሁለት የመስክ ድጋፋዊ ክትትል የተደረገ ሲሆን በ2000 ዓ/ም ለሚከናወኑ ተግባራት የጋራ መግባባት ተፈጥሯል።

6. የወረዳ መልካም አስተዳደር ፓኬጅን ለማስፈጸም ከተዘጋጁ ህጎች ውስጥ የቀበሌ ካቢኔ አደረጃጀት ፣ የልማት ኮሚቴ አደረጃጀትና የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ ተዘጋጅቶ የካብኔ አስተያት ከተሰጠ በኋላ በቢሮው ጸድቆ ተሰራጭቷል ። በመተግበር ላይ

የሚገኝ ሲሆን የሥራ አስኪያጅ አቀጣጠርን በተመለከተ ግብረ መልስ በመሰብሰብ ላይ ይገኛል ። የማህበራዊ ፍርድ ቤት አፈጻጸምን የሚያሻሽል አዋጅ ተዘጋጅቶ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ቀርቦ በመተቸት ላይ ነው ።

## በሴክተሩ የገጠር ወረዳና ቀበሌ መልካም አስተዳደር አፈጻጸምን በተመለከተ፡-

### 1. የአመራር ባለቤትነትን ማጠናከር ፡-

- የክልሉ አመራር በፖኬጅ ሰነድና የማስፈጸሚያ መመሪያዎች ላይ ተወያይቶ ሊስተካከሉ የሚችሉ አሰራሮችን በማሻሻል ተግባራዊ እንዲደረግ የወሰነ ከመሆኑም በላይ በባለቤትነት እየመራው ይገኛል ፡፡

### 2. የፖኬጅ ማስፈጸሚያ መመሪያዎች ህጎችና ቅጻቅጾች ዝግጅትና ትግበራ፡-

- በአጠቃላይ 9 መመሪያዎችና ከ6 በላይ ቅጻቅጾች ተጠናቀው ለካብኔ ቀርበው የማስተካከያ ሃሳብ ተሰጥቶበት በአቅም ግንባታ ቢሮ ተስተካክሎ በተግባር እንዲውል ተወስኗል ፡፡ በዚሁ መሠረት የቀበሌ ካቢኔ አደረጃጀት፣ የቀብሌ ኮሚቴዎች አደረጃጀት የቀበሌ ሠራ አስኪያጅ ቅጥርና የቀበሌና የወረዳ ሱፐርቪዥንና ኤንስፔክሽን ቡድን መዋቅርና መመሪያዎች ተዘጋጅተው የተሰራጩ ሲሆን የሌሎች መመሪያዎች የማስተካከያ ሥራ በመከናወን ላይ ነው ፡፡ እንደተጠናቀቀም ለፈጻሚ አካላት ይሰራጫል ፣ ተግባራዊም ይደረጋል ፡፡

### 3. በፖኬጅ ሰነድ ላይ የተሰጠ ሰልጠና ፡-

- ቀደም ሲል በክረምቱና በዓመቱ መጨረሻ እስከ ቀበሌ ለሚገኝ የአመራር አካል ስልጠና የተሰጠ ቢሆንም በየደረጃው የአደረጃጀት ለውጥ በመደረጉና የአመራር መቀያየር የተፈጠረ በመሆኑ ድጋሚ ስልጠና መስጠት አስፈላጊ ይሆናል ፡፡ በመሆኑም ከዞንና ከልዩ ወረዳ ለተውጣጡ 92 የአመራር አካላት የአሰልጣኝ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን እነዚህ አሰልጣኞች ከወረዳ ለተውጣጡ አዳዲስ ሰልጣኞች ስልጠና እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ የአስልጣኞች ስልጠና የወሰዱት ደግሞ በየደረጃው ለሚገኝ የመንግሥት ሠራተኞና የህብረተሰብ አባላት በወጥነት ሥልጠና እንዲሰጥ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በወቅቱ በተለያየ ምክንያት ያልተሰጠ በመሆኑ በ2000 ዓ/ም ስልጠናው በወጥነት እንዲሰጥ ይደረጋል ፡፡

## *4. አደረጃጀትና አሰራርን ማስተካከል ፦*

❖ ***የቀበሌ ካብኔ ፦***

የቀበሌ ካብኔ 7 እንዲሆን የተወሰነ ሲሆን ከሀዲያ ዞን በስተቀር በአደረጃጀት ማስተካከል ተደርጓል፡፡ ከቀበሌ በታች የነበሩ አደረጃጀቶችም በሁሉም ደረጃ ማስተካከያው ተከናውኗል ፡፡ አሰራሩና አፈጻጸሙ ሁሉም መመሪያዎች እንደተሰራጩ ተጨማሪ ስልጠና ለአመራሩ ለመስጠት ታወዷል ፡፡

❖ ***የኢንስፔክሽንና የእቅድ ቡድን አደረጃጀት ፦***

በክልሉ የሲ/ሰ/ኤጀንሲ ቋሚ መደብና የሥራ ዝርዝር ተዘጋጅቶ ከጸደቀ በኋላ ወደየወረዳው የተላከ ሲሆን በሲዳማ ዞን አደረጃጀቱ ተስተካክሎ ወደ ተግባር የተገባ ሲሆን በሌሎች ወረዳዎች የአደረጃጀት ሥራ በመሠራት ላይ ይገኛል፡፡

❖ ***የቀበሌ ጽ/ቤት ኃላፊ መቅጠር***

በቀበሌ ደረጃ አጠቃላይ ሥራዎችን የሚያከናውን ሥራ አስኪያጅ እንዲቀጠር በካብኔ የተወሰነ ሲሆን የቀበሌ አመራር ክፍያም ቅጥሩ እንደተፈጸመ እንዲቆም ተወስኗል፡፡ በመሆኑም የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ ተቀጥሮ ሙሉ ቀን ቀበሌዎች ለህዝብ አገልግሎት እንዲሰጡ የተወሰነ ሲሆን የምልመላ ሥራ በመከናወን ላይ ነው ፡፡ ስራ አስኪያጁ የጉዳይ ተቀባይን ሥራንም ደርቦ እንዲሰራ ተወስኗል ፡፡

❖ ***የሞዴል አርሶ አደር ቀበሌና ወረዳ ምርጫ ፦***

በፖኬጁ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት ምርጫ ማከናወን የሚጠበቅ ሲሆን በተወሰኑ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ቀደም ሲል በነበረ አሰራር ምርጫ ተከናውኖ በክልልም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ የተወሰኑ አርሶ አደሮች ተሸልመዋል ፡፡ ይሁን እንጂ ምርጫው በፖኬጁ ላይ በተቀመጠው መስፈርት ባለመሆኑ መስፈርቱን መሠረት ያደረገ ምርጫ እንዲከናወን መመሪያ ተላልፎ ማስተካከያ በመደረግ ላይ ነው ፡፡ ነገር ግን ሥራው እየተከናወነ ቢሆንም በተሟላ መንገድ በቀጣዩ ዓመት መጀመሪያ ይፈጸማል ተብሎ ይጠበቃል ፡፡

❖ ***የቀበሌ ኮሚቴዎችን መልሶ ማደራጀት ፡-***

ቀደም ሲል በየቀበሌው ከ20 በላይ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ያሉ በመሆኑ በፖኬጁ በተቀመጠው መሠረት ወደ 4 ኮሚቴዎች የማደራጀት ሥራ በአብዛኛው ቀበሌዎች የተከናወነ ሲሆን በቀሪዎቹ የሀድያ ዞን ቀበሌዎች ደግሞ በመከናወን ላይ ይገኛል ፡፡

## 4. ***የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ የመልካም አስተዳደር ሥራን በተመለከተም፡-***

❖ በክልል ደረጃ የICT ቡድን ተቋቁሞ በመሥራት ላይ ይገኛል ፡፡

❖ የወረዳኔት እና School net (ስኩል ኔት) የጎደሉ ዕቃዎች የመለየት ሥራ ተከናውኖ ለICT ኤጀንሲ ተላልፏል ፡፡

❖ በ102 ወረዳዎች ኢንተርኔትና የስልክ አገልግሎት ይሰጣል ፡፡

❖ ለ60 ወረዳዎች በአስተማማኝ ሁኔታ ቪዲዮ ኮንፈረንስ እንደሚሰጥ ተረጋግጧል ፡፡

❖ የወረዳ ኦፐሬተሮች ቀደም ብሎ የታቀዱ ሲሆን ለ3ኛ ጊዜ የ1 ወር ስልጠና ወስደዋል ፡፡ በተጓደሉበትም የማሟያ ቅጥር በማከናወን መረጃ በመሰብሰብ ላይ ነው፡፡

❖ በክልል ደረጃም ሆነ ከ25 በላይ በሆኑ ወረዳዎች ተጠቃሚዎችን ለICT ማሰልጠን ተጀምሯል፡፡ በዚሁ መሠረት 2509 ሠልጣኞች የመሠረታዊ ICT ስልጠና ወስደዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ 1500ዎቹ በወረዳ በሚገኙ የወረዳ ኔት ኦፐሬተሮች የተሰጠ ስልጠናዎች ናቸው ፡፡

❖ በእያንዳንዱ ወረዳ አራት አራት እና በዞኖች ሶስት ሶስት ኮምፒውተር ተሰራጭቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ ነው ፡፡ በቀጣይም ተጠናክሮ የሚቀጥል ተግባር ነው፡፡

- በክልል ደረጃ ለሁሉም ከዞንና ከወረዳ ለተውጣጡ ሶስት ሶስት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የInternet አጠቃቀም ስልጠና ለስድስት ተከታታይ ዙር እንዲሰት ተደርጓል ፡፡

## 5. *SPM ROP እና BPR*

- በክልልለ ደረጃ ስትራቴጂክ ዕቅድ ፣ ውጤት ተኮር የአፈጻጸም መመሪያና የአሰራር ስርዓት ማሻሻያ ሰነድ ተሻሽሎ ተዘጋጅቷል ፡፡

- ሰባት ወረዳዎችና በወረዳዎቹ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና መሥሪያ ቤቶች ለትግበራ የተመረጡ ሲሆን የቴክኒክ ኮሚቴም ተቋቁሟል ፡፡ ከዞንና ከልዩ ወረዳ ለተመረጡ 92 አሰልጣኞችና ለክልል መ/ቤት ኃላፊዎች ስልጠና ተሰጥቷል ፡፡ ይሁን እንጂ የመመሪያ ለውጥ በመደረጉ በፓኬጅ ላይ በተቀመጠው መሠረት በወረዳዎች ሥልጠና አልተጀመረም ፡፡

- ሌሎች አጫጭር ስልጠናዎችን በተመለከተ የስልጠና ሰነዶች እየተዘጋጁና የማሻሻል ሥራ እየተከናወነ ነው ፡፡ ሥራው ሲጠናቀቅ የህትመት ሥራ ተከናውኖ በየደረጃው ስልጠና ይሰጣል ፡፡

- የዳኛና ዐቃቢያነ ህግ ባለሙያዎችን በተመለከተ ምልመላው ተጠናቆ 301 ሰልጣኞች ስልጠና የጀመሩ ሲሆን በቀጣይም ተጠናክሮ የሚቀጥል ተግባር ነው ፡፡

## 4. የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ የአቅም ግንባታ ፕሮግራም

የመንግሥትንና የማስፈጸም አቅም ከማጎልበት አንጻር ዘመናዊ ኢንፎርሚሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን መጠቀም ወሳኝ የጊዜው ጥያቄ ከመሆኑም አንጻር ቴክኖሎጂውን ለመቀም የሚያግዙ ቁሳቁሶች /ኮምፒውተር ፣ ተዛማጅ ዕቃዎች የማሟላት እንዲሁም በቁሳቁስ ለመጠቀም የሚያስችል እውቀትና ክህሎች መፍጠሪያ ስልጠናዎች በስፋት ተሰጥተዋል ፡፡ ለነባር ወረዳዎች እያንዳንዳቸው አራት አራት ኮምፒውተሮችና ተዛማች ዕቃዎች እንዲደርሳቸው ከመደረጉም በላይ ሁሉም ዞኖች

ሶስት ሶስት ኮምፒውተሮችና ተዛማች ዕቃዎች እንዲደርሳቸው ተደርጓል ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በክልል የሚገኙ 25 ቢሮዎችና ሲቪክ ድርጅቶች( ሴቶችና ወጣቶች) ልዩ ልዩ መሣሪያዎች እንዲያገኙ ተደርጓል ፡፡ ከ65% በላይ በሚሆኑ ወረዳዎች Point to point video conference አገልግሎት የሙከራ ሥርጭት ተደርጓል ፡፡ ለአገልግሎትም ብቁ ሆነዋል ፡፡ በዚህ በኩል ቴክኖሎጂው የፈጠረውን አመቺ ሁኔታዎች በሙሉ አሟጦ የመጠቀም የእውቀትና ክህሎት ችግር በአመራሩ በኩል መኖሩ ተረጋግጦ አመራሩን በቴክኖሎጂው አጠቃቀም ላይ የማሰልጠን ሥራ ተጀምሯል ፡፡ በሚቀጥሉት 6 ወራትም የሪፖርትና የመረጃ ልውውጥ በe-mail እንዲሆን ቀጣይ ስልጠናዎችና ተግባራት በመከናወን ላይ ናቸው፡፡ በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ፕሮግራም የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራትም የሚከተለውን ይመስላል ፡፡

1. ለ30 የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን አካላትና ለ45 የኦዲት ቢሮ ሠራተኞች በመሠረታዊ ኮምፒውተር አፕልኬሽንና ኢንተርኔት አጠቃቀምና ለኦዲት ቢሮ በፒችትሪ አካውንቲንግ ስልጠና ተሰጥቷል ፡፡

2. ለከተማ ልማት ፣ ለቤቶች ኤጀንሲ ፣ ለመካከለኛ አመራሮችና ለጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት አገልግሎት ከ20 ጊዜ በላይ የቪዲዩ ኮንፈረንስ አገልግሎቶች እንዲያገኙ ተደርጓል ፡፡

3. ለ179 የወረዳኔት ባለሙያዎች በሁለት ዙር በኔት ወርኪንግ ፣ በመረጃ አያያዝና በኮምፒውተር ጥገና ለ1 ወር ስልጠና ተሰጥቷል ፡፡

4. ለወረዳዎችና ለተለያዩ ክልል ቢሮዎች 18 ኮምፒውተሮች ፣ 21 ላፕቶፖችና 2 ፕሮንተሮች የጥገና አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን በዚህ አገልግሎት ከ200 ሺህ ብር በላይ ወጪ እንዲቀንስ ተደርጓል ፡፡

5. ለ250 የወረዳ አመራሮች በኮሙዩኒቲ ኢንፎርሜሽን ሲስተም ማቋቋሚያና አጠቃቀም ስልጠና ተሰጥቷል ፡፡

6. የማህበረሰብ መረጃ ሥርዓት ለማቋቋም 60 የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች ተዘጋጅተው ለኢንፎርሜሽን ኪሙኒኬሽን ባለሥልጣን የተላለፈ ሲሆን ለ5 ወረዳዎች የመለስተኛ ሬዲዮ ጣቢያና የኢኮቴ ማዕከል ምስረታ ምላሽ ተደርጓል፡፡

7. የአቀም ግንባታ ቢሮ ድህረ ገጽ ተዘጋጅቶ በአየር ላይ ውሏል ፡፡

8. ለፀረ-ሙስናና ሥነ-ምግባር ቢሮ የዳታ ቤዝ ተሰርቶ አገልግሎ በመስጠት ላይ ይገኛል ፡፡

9. ከ65% በላይ በሚሆኑ ወረዳዎች የPoint to point video conference አገልግሎት የሙከራ ስርጭት ተደርጎ ለአገልግሎት ብቁ ሆነዋል ፡፡ ከ80% በላይ ወረዳዎች ደግሞ የICT የሳተላይት ተሌፎንና የኢንተርኔት ተጠቃሚ ሆነዋል ፡፡ ከ300 በላይ ከዞን ፣ ወረዳ የሚገኙ የአቅም ግንባታ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በ6 ዙር የኢንተርኔት አጠቃቀም ስልጠና አግኝተዋል ፡፡

10. በክልሉ የንግድና ኢንዱስተሪና ገቢዎች ባለሥልጣን ቢሮዎችን እስከ ወረዳ በlocal area net work ለማገናኘት የጨረታ ሰነድ ተዘጋጅቶ በዓለም ባንክ ይሁንታ አግንቷል፡፡

11. ከ2509 በላይ ከክልል - ወረዳ የሚገኙ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የመሠረታዊ የኮምፒውተር አጠቃቀም ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል ፡፡ 25 የክልሉ ወረዳዎች አመራሮችንና ባለሙያዎችን የማሰልጠን ሥራ ጀምረዋል፡፡

12. ስምንት የተለያዩ የመሠረታዊ ኮምፒውተር ስልጠና የማሰልጠኛ ሰነዶች በቢሮው ባለሙያዎች ተዘጋጅቶ ለየወረዳ የቴክኒክ ባለሙያዎች ተሰራጭቶ ስልጠና በመስጠት ላይ ነው ፡፡

13. የ2000 ዓ/ም የፒስካፕ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለፌዴራል አቅም ግንባታ ሚኒስቴር ተልኳል ፡፡

14.በፌዴራል የICT ባለሥልጠን በተዘጋጀ የ Net Working እና የጥገና ስልጠና ላይ ከወረዳና ከክልል የተውጣጡ 15 ባለሙያዎች የአንድ ወር ስልጠና አግንተዋል፡፡

15.በክልሉ በሚገኙ ወረዳዎች የሚገኙና የጎደሉ እንዲሁም ለአዳዲስ ወረዳዎች የሚያስፈልጉ የICT ዕቃዎች መረጃ ተጣርቶ ለፌዴራል የICT ባለሥልጣን ተልኳል ፡፡

16.የክልሉ ውሃ ቢሮ የብሮንድ ባንድ መስመር ተጠቃሚ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን በከፍተኛ ወጭ ተሰርቶ አገልግሎት መስጠት ያልቻለው የቢሮው Network እንደገና በICT ባለሙያዎች ተሰርቶ ቢሮው ተጠቃሚ እንዲሆን ተደርጓል ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በፒስካፐ የሚከናወኑ ልዩ ልዩ ተግባራት ውስጥ በየደረጃው የሚገኙ አስፈጻሚ አካላትን አቅም በማጎልበትና አሰራሮችን ለማስተካከል የሚያስችሉ መመሪያዎችን በማሳተምና ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ በመልካም አስተዳደር አፈጻጸም እገዛ እንዲኖራቸው ከሚመለከታቸው የክልል ሴክተር ቢሮዎች ጋር በመተባበር የሚከተሉት ተከናውነዋል፡፡

ሀ/ 812 ለሚሆኑ ከወረዳ እስከ ክልል ለሚገኙ የውስጥ ኦዲተሮች ከ15-20 ቀን በ3 ዙር ስልጠና እንዲውስዱ የተደረገ ሲሆን ከ1800 በላይ የኦዲት መመሪያና የማሰልጠኛ ማንዋል ታትሞ በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ እንዲሰራጭ ተደርጓል ፡፡

ለ/ ከ580 በላይ ለሆኑ የከተማ ልማት ቢሮና ከተማ አስተዳደሮች ከ15-20 ቀን ስለ ከተማ መልካም አስተዳደርና የከተማ አቅም ግንባታ ፕሮግራም ልዩ ልዩ መመሪያዎችና የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም ስልጠናበ2 ተከታታይ ዙር እንዲሰጥ ተደርጓል ፡፡

ሐ/ ከከተማ አቅም ግንባታ ፕሮግራም ጋር በፒስካፐ ተጠቃሚ ለሆነው የክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ማስፈጸሚያ መመሪያዎች በ70 ሺህ ኮፒ

በላይ በማተሚያ ቤት ታትሞ ለቢሮው ተልኮ አገልግሎት በመስጠት ላይ ነው፡፡

መ/ 86 ከወረዳ እስከ ክልል የሚገኙ የገቢዎች ባለሥልጣን ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በታክስ ኦዲት ሙያ ለ15 ቀናት ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከየዞኑና ከተማዎች የተመረጡ 10 የታክስ ባለሙያዎች በቫት አፈጻጸም ሙያዊ ስልጠና እንዲያገኙ ከኢትዮጵያ ሥራ አመራር ጋር በተገበው ውል መሠረት በአዲስ አበባ ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል ፡፡ 400 የታክስ ባለሙያዎችም ስለገቢ አሰባሰብባና ተዛማጅ ፖሊሲዎች ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል ፡፡

ሠ/ የክልሉ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎችም በመንግሥት ልዩ ልዩ ፖሊሲዎችና በመልካም አስተዳደር ፖኬጅ ላይ የ10 ቀናት ስልጠና ከክልሉ ምክር ቤት ጋር በመተባበር እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን ስለመልካም አስተዳደር ፓኬጅ አፈጻጸምም ስልጠና ተሰጥቷቸዋል ፡፡ 150 የወረዳና የዞን ም/ቤት ቋሚ ኮሚቴ አባላትም ተመሳሳይ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል ፡፡

ረ/ የክልሉ ፀረ-ሙስናና ሥነ-ምግባር ኮሚሽን ልዩ ልዩ መመሪያዎችና ትምህርታዊ ጽሁፎችን በክልሉ በሚገኝ የFm 100.9 ሬዲዮ ጣቢያ ዓመቱን ሙሉ መልዕክት በማስተላለፍ የህብረተሰቡን ግንዛቤ እንዲያጎለብት የተደረገ ሲሆን ልዩ ልዩ ፖስተሮች ፣ ብሮሼሮችና መጽሄቶችም አሳትሞ እንዲያሰራጭ ተደርጓል ፡፡ በገቢ አሰባሰብና በታክስ አፈጻጸም የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማዳበር እንዲቻልም የገቢዎች ባለሥልጣን ስለ ታክስ አሰራርና አፈጻጸም፣ ከህብረተሰቡ ስለሚጠበቁ ተግባራት በFm 100.9 ሬዲዮ ጣቢያ ትምህርታዊ መልዕክት በየሳምንቱ እንዲያስተላልፍ በመደረግ ላይ ነው ፡፡

በሴክተሩ ከተፈጸሙት ተግባር ውስጥ ጥሩና አበረታች ለሌሎች ክልሎች ጭምር በአርያነት ሊጠቀስ የሚገባው የፒስካኘ (Public Sector Capacity building

program) በጀት አጠቃቀም ላይ ያለው ሁኔታ ነው፡፡ ኘሮግራሙ የማስፈፀም አቅማችንን ለማጎልበት ያለብንን የፋይናንስ እጥረት ከመቅረፍ አንጻር ያለውን ፋይዳ በአግባቡ የመገንዘብ በተደረገው ጥረት ኘሮግራሙ የሚጠይቀውን አድካሚ የገንዘብ ሰጭዎችን ውጣ ውረድ በአግባቡ በመቋቋም በተደረገው ጥረት በዘመኑ መጠቀም ከሚገባን በጀት ከ90% በላይ መጠቀም ተችሏል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ሥልጠናዎችንና በዚሁ ኘሮግራም በጀት መሸፈን ከመቻላችንም በላይ ለበርካታ ቁሳሱሶች ግዥና መመሪያዎች ህትመትና ሥርጭት ማዋል ተችሏል፡፡

በጥቅሉ በሴክተሩ በዓመቱ ልናስለካ ያሰብናቸውንና ግቦች ከሞላ ጎደል ማሳካት ችለናል፡ በሂደቱ በተነፃፃሪ የተሻለ የማስፈፀም አቅም መገንባት አስችሎናል፡፡ ሆኖም ሥራው የሚጠይቀው ከፍተኛ ተነሳሽነት ተከታታይና ያልተቋረጠ ድጋፍና ክትትል እንዲሁም የሁሉም ባለ ድርሻ አካላት የባለቤትነት መንፈስ ከመፍጠር አንጻር በየደረጃው ካለው አመራራችን ጀምሮ ያለው ጉድለት ለማስወገድ ተከታታይ ሥራና ጥረትን የሚጠይቅ መሆኑን በየጊዜው የተደረጉ ግምገማዎች ያሣዩትን በመሆኑ በዚህ በኩል ወሳኝ ቀሪ ሥራዎች እንዳሉብን፡፡